# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና

# ኤጀንሲ

## ኤች አይቪ/ኤድስ በስራ ቦታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተዘጋጀ

## የአፈፃፀም ማኑዋል

አዲስ አበባ

ኅዳር 2013

# የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ
# ኤች አይቪ/ኤድስ በስራ ቦታ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተዘጋጀ የአፈፃፀም ማኑዋል

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት አንቀፅ 42/2 እና በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 ተሻሽሎ የወጣው 1064/2010 መሠረት ማንኛውም ሠራተኛ ጤናማና አደጋ የማያስከትል ምቹ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት ያለው በመሆኑ፣

ሀገራችንን ከድህነት በማላቀቅ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለማሰለፍና ድህነትን ተረት ለማድረግ በሚካሄደው ርብርብ የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የሚጠበቅበትን ድርሻ ለመውጣት በምንም የማይተካ ሚና የሚጫወተውን የሰው ኃይል የሚያሳጣ በሽታ አሳሳቢ የሥራ ቦታዎች የልማት ችግር መሆኑን በመገንዘብ፣

በተፈጥሮ፣በኢኮኖሚና በማህበራዊ ችግሮች ምክንያት ለኤች አይቬ ኤድስ ወረርሽኝ ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ልዩ ትኩረት ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲን ተልእኮ ለማሳካትና ራእይን እውን ለማድረግ እንዲቻል ሠራተኞችን ከኤች ኤይቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ለመከላከልና ኤች አይቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለና ህሙማን ሠራተኞች ምንም ልዩነት ሳይደረግባቸው ሰብዓዊ መብታቸው ተጠብቆ ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ እየተደረገላቸው ውጤታማ ሆነው እንዲቀጥሉ ማስቻል ወሳኝ መሆኑን በመረዳት፣

ይህ የኤች አይቪ/ኤድስ የሥራ ቦታ መከላከያና መቆጣጠሪያ ማስፈፀሚያ ማኑዋል ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

1.1.1 ይህ ማኑዋል ‹‹ የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የኤች አይቪ ኤድስ የሥራ ቦታ መከላከያና መቆጣጠሪያ ማስፈፀሚያ ማኑዋል›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2.ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ማኑዋል ውስጥ

2.1. **‹‹መሥሪያ ቤት››** ማለት የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ መ/ቤት ሲሆን የሪጅን ጽ/ቤቶችን ፣ ቅ/ጽ/ቤቶችንም እና መስክ ጽ/ቤቶችንም ያጠቃልላል፡፡

2.2. **‹‹ሠራተኛ››** ማለት በማህበራዊ ዋስትና ኤንጀንሲ ዋና መ/ቤት፣ በሪጅን ጽ/ቤትና ቅ/ጽ/ቤት መስክ ጽ/ቤት ተቀጥሮ የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ቋሚ ሠራተኛ የሆነ ሲሆን ለዚህ ማኑዋል አፈፃፀም ቢያንስ አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ በኤጀንሲው መ/ቤት በኮንትራት ተቀጥሮ በማልገል ላይ ያለ ሠራተኞችንም ያጠቃልላል፡፡

2.3. **‹‹ከፍተኛ አመራር›** የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ወይም ምክትል ዋና ዳይሬክተር ናቸው፡፡

2.4. **‹‹መካከለኛ አመራር ማለት››**አጀንሲዉን ዳይሬክቶሬቶች፣ የሪጅን ጽ/ቤት ፣ቡድኖች እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በኃላፊነት የሚመራ ሰዉ ነዉ፡፡

2.5. **‹‹ የሥራ ቦታ››** ማለት የመ/ቤቱ ሠራተኞች ሥራቸውን የሚያከናውኑበት መደበኛ ሥፍራ ሲሆን እንደአግባቡ በመስክ የሥራ ማከናወኛ ስፍራንም ይጨምራል፡፡

2.6. **‹‹ኤች አይቪ/ኤድስ››** ማለት በሰውነት ውስጥ በሽታን የመቋቋም ኃይልን በማዳከምሙሉ በሙሉ የኤድስ ህመምተኛ እንዲሆን የሚያደርግ ህዋስ ወይንም ቫይረስ ነው፡፡

2.7. **‹‹ ኤድስ››** ማለት በኤች አይ ቪ/ ኤድስ ሳቢያ ሰውነት በተፈጥሮ ያለውን በሽታ የመከላከል አቅም በማዳከም ወይም በሌላ በማንኛውም ተደራቢ በሽታ አምጪ ህዋስ ከተያዘ በኋላ የሚከሰት በሽታ መገለጫ ነው፡፡

2.8. **‹‹ኤች አይቪ/ኤድስ በደሙ ውስጥ የተገኘ››** ማለት የጤና ምርመራ ለማድረግ ህጋዊ ፈቃድ ለተሰጠው ተቋም/ድርጅት የደም ናሙና ሰጥቶ

በተደረገው የምርመራ ውጤት ኤች አይቪ/ኤድስ ቫይረሱ በደሙ ውስጥ ስለመኖሩ በመረመረው ተቋም በጽሁፍ ተረጋግጦ ማስረጃ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

2.9. ‹‹**የኤድስ ህመምተኛ**›› ማለት በደሙ ውስጥ ኤች አይቪ/ኤድስ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ለማረጋገጥ በሚደረገው የደም ምርመራ በደሙ ውስጥ የኤች አይቪ ቫይረስ ያለበት መሆኑ የተረጋገጠ እና በተጓዳኝ በሽታ አማካይነት ታማሚ የሆነ ነው፡፡

2.10. ‹‹**ቅድመ ምርመራ የምክር አገልግሎት**›› ማለት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይቪ የደም ምርመራ ከመደረጉ በፊት ተመርማሪው ለምርመራው የተነሳበትን ዓላማ መሠረት በማደረግ የምርመራው ውጤት በቀጣይ ህይወቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያስከትል ሥነ ልቦናዊ ዝግጅት እንዲያደርግ የሚያግዝ የባለሙያ ምክር ነው፡፡

2.11. ‹‹**ድህረ ምርመራ የምክር አገልግሎት** ›› ማለት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች አይቪ ምርመራ ላደረገ ሰው የምርመራ ውጤቱን መሠረት በማድረግ በባለሙያ የሚሰጥ የምክር የሥነ ልቦና ድጋፍ ነው፡፡

2.12. ‹‹ **የአባላዘር በሽታ**›› ማለት በግብረ ስጋ ግንኙነት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው በረቂቅ ህዋስ አማካኝነት የሚተላለፍ ሲሆን ጨብጥ፣ ክርክር ባምቡሌ፣ ቂጥኝ እና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡

2.13. ‹‹**ድጋፍና እንክብካቤ**›› ማለት ኤች አይቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ላለና የኤድስ ሕሙማን ሠራተኞች ሥራቸውንን ሕይወታቸውን በተሻለ ሁኔታ እንዲመሩና የቫይረሱን ስርጭት በመቀነስ ረገድ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያግዝ ሰብዓዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሥነ- ልቦናዊ ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባር ነው፡፡

2.14. ‹‹**ምስጢር**›› ማለት አንድ ሰው የምርመራ ውጤቱ ወይም የህመሙ ሁኔታ ከኤች አይቪ/ኤድስ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያመለክተው የህክምና ሪከርድ ማወቅ ከሚገባቸው ባለሙያዎች ውጭ ከሠራተኛው/ዋ ፍቃድ ውጪ ግልጽ የማይወጣበት ሥርዓት ነው፡፡

2.15. .‹‹**የመከላከል ተግባር**›› ማለት የኤች አይቪ/ኤድስ በደሙ ውስጥ ከሚገኝበት አንድ ሰው ወደ ጤነኛው ሰው እንዳይዛመት ተገቢ ጥንቃቄ የማድረግ

ተግባር ሲሆን በሽታውን ለመከላከል የሚረዳ ማንኛውም የማስተማርና ሌሎች ተግባሮችን ያካትታል፡፡

2.16. ‹‹**መቆጣጠር**›› ማለት የኤች አይቪ/ኤድስ ቫይረስን ሥርጭት እና ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ባለበት ለማቆም የሚወሰድ የመከላከል ተግባርና የክትትል እርምጃ ነው፡፡

2.17. ‹‹**ምቹ የሥራ ሁኔታ**›› ማለት የሥራ ላይ ህመም፣ የሥራ ላይ ጉዳት፣ የፆታ ትንኮሳ፣ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚገኝ ሰዎችን ጤና፣ እና ሞራል ከሚነኩ የማግለልና አድሎአዊ ድርጊቶች የፀዳ የሥራ ሁኔታን የሚያጠቃልል ነው፡፡

2.18. ‹‹**መረጃ**›› ማለት ኤች አይቪ/ኤድስን አስመልክቶ በሁሉም ዘንድ በግልጽ ሊታወቅ የሚገባቸው አህዛዊ ጥንቅር ወይም ንድፈ ሃሳባዊ ንፅፅርን ትንታኔ የያዘ ወቅታዊ ሰነድ ነው፡፡

2.19. ‹‹ **በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ምርመራ**›› ማለት ተመርማሪው በራሱ ተነሳሽነት ኤች አይቪ በደሙ ውስጥ መኖሩን ወይም አለመኖሩን በህክምና ተቋም ወይም ኤች አይቪ ምርመራ በሚደረግበት የህክምና ቦታ የሚያደርገው ምርመራ ነው፡፡

2.20. በዚህ ማኑዋል በወንድ ጾታ የተገለፀው ለሴትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ ማኑዋል ዓላማ በሀገር አቀፍ ደረጃ ኤች.አይቪ/ ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚነደፉትን ፕሮግራሞች ወይም ዕቅዶችን በዚህ ማኑዋል በኤጀንሲው ተግባራዊ በማድረግ

3.1 ጤንነቱ የተጠበቀ ኣና አምራች ሠራተኞችን እንድሆን ምቹ የሥራ አካባቢ መፍጠር ፣

3.2 በኤች አይቪ / ተጋላጭነትን መቀነስና ተጎጂዎችን በመደገፍ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ልዩ ትኩረትና ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት መዘረጋት፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ማኑዋል በማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ኤች አይቪ/ኤድስ የሚያስከትለውን ተፅእኖ

## ለመከላከልና ለመቆጣጠር ስለሚከናወኑ

## ተግባራት እና ኃላፊነቶች

### 5. በመ/ቤቱ ውስጥ ስለሚከናወኑ ተግባራት፡-

5.1. ኤች አይቪ/ኤድስ የሥራ ቦታና አጠቃላይ አገራዊ የልማት ችግር መሆኑን በመቀበል ወረርሽኙ በኤጀንሲው ተልእኮ አፈፃፀምና በሠራተኞች ኑሮ ላይም የሚያስከትለውን ዘርፈ ብዙ ተፅእኖ ለመቋቋም በባለቤትነት ስሜትና በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ፣

5.2. የጤንነትና የደህንነት ፕሮግራሞችን በመንደፍና በመተግበር የኤጀንሲው የስራ ቦታዎች ምቹና ጤናማ እንዲሆኑ ማድረግ፣

5.3. በኤጀንሲው የኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ ሠራተኞችንና ሌሎች ተባባሪ አጋር አካላትን ያቀፈ ዘላቂ ተቋማዊ አደረጃጀት ያለው በዕቅድና በበጀት የሚመራ፣ ግልፅ አሳታፊ ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራር መፍጠር፣ኤች አይቪ/ኤድስን የአባላዘር በሽታዎችና የስነ ተዋልዶ ጤናን የሚመለከት ወቅታዊ መረጃ ማቅረብ እንዲሁም የመከላከልና የመቆጣጠሩን አጠቃላይ ፕሮግራም ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት መዘርጋት፣

5.4. በኤጀንሲው ኤች አይቪ/ኤድስን ሌሎች የአባላዘር በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚነደፍ ማንኛውም ፕሮግራም በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መርህ ላይ የተመሠረተ የሴቶችን ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት የሚያጎለብት ማድረግ፣

5.5. በተፈጥሮአዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ምክንያት ለኤች አይቪ ስርጭት ይበልጥ ተጋላጭ ለሆኑ አካል ጉዳተኞች ሠራተኞች ልዩ ትኩረት መስጠት፣

5.6. አጠቃላይ ሠራተኛው ስለኤች አይቪ/ኤድስ ወረርሽኝ ያለውን ግንዛቤ ለማሳደግ አለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያገኙ ዘዴዎች በመጠቀም ትምህርት እንዲሰጥ ማድረግ፡

5.7. በሥራ ላይ ያሉ ሠራተኞች እና በኤጀንሲው ለመቀጠር የሚቀርቡ ሥራ ፈላጊ አመልካቾች የኤች አይ ቪ ምርመራ እንዲያደርጉ አለማስገደድ፣

5.8. የኤጀንሲው ሠራተኞች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይቪ ምርመራ እንዲያደርጉ ማበረታታት፣ የምርመራ ውጤቱም ሠራተኛው እንዲታወቅ ካልፈቀደ በስተቀር በምስጢር ጠብቆ መያዝ፣

5.9. ኤች አይቪ በደማቸው ውስጥ ያለና የኤድስ ሕሙማን የኤጀንሲው ሠራተኞች ሥራ ፈላጊ አመልካቾች ላይ ምንም አይነት መድልዎና መገለል አለማድረግ፣

5.10. አግባብ ያለው የኤጀንሲው አስተዳደራዊ መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኤጀንሲው ሠራተኛ ኤች አይቪ በደሙ ውስጥ በመኖሩ ወይም የኤድስ ሕመምተኛ በመሆኑ ምክንያት ብቻ የሥራ ውሉ እንዲቋረጥ ያለማድረግ፣

5.11. ኤች አይቪ በደማቸው ውስጥ ላለና ኤድስ ሕሙማን ለሆኑ የኤጀንሲው ሠራተኞች አቅም በፈቀደ መጠን አስፈላጊውን ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣

## 6. የኤጀንሲው በየደረጃው ያሉት አመራሮች ተግባርና ሃላፊነት

6.1. የኤጀንሲው **ከፍተኛ አመራር** የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ. ኤች አይቪ/ኤድስ የሥራ ቦታዎች የልማትና ሊሰጥ ስለሚገባው የተቀላጠፈ አገልግሎት አሰጣጥ ዋና ችግር መሆኑን በመገንዘብ ወረርሽኙ ለመግታትና የኤጀንሲው ተልእኮና አፈፃጸም እንዲሁም በሠራተኛው ኑሮ ላይ የሚያስከትለውን ዘርፈ ብዙ ተፅእኖ ለመቋቋም ግንባር ቀደም በመሆኑ ቁርጠኝነት የተሞላበት አመራር መስጠት፡

ለ. በብሔራዊ የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፖሊሲ በመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሥራ ቦታዎች የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሕጎች እና በዚህ መመሪያ መሠረት የኤች አይቪ/ኤድስ ወርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያደርጉትን ሥራዎች በበላይነት መቆጣጠር፣

ሐ. የፀረ ኤች አይቪ/ኤድስ ግብረ ኃይል ማቋቋም፣

መ. የኤች አይቪ/ኤድስ ፈንድ ማቋቋም. በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን መከታተል፤

ሠ. የፈንዱን የወጪና የገቢ ጊዜዉን ጠብቆ ኦዲት መደረጉን ማረጋገጥ፤

6.2 የኤጀንሲው **መካከለኛ አመራር** የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ. ኤች አይቪ/ኤድስ የሥራ ቦታዎች የልማትና ሊሰጥ ስለሚገባው የተቀላጠፈ አገልግሎት አሰጣጥ ዋና ችግር መሆኑን በመገንዘብ ወረርሽኙ ለመግታትና የኤጀንሲው ተልእኮና አፈፃጸም እንዲሁም በሠራተኛው ኑሮ ላይ የሚያስከትለውን ዘርፈ ብዙ ተፅእኖ ለመቋቋም ግንባር ቀደም በመሆኑ ቁርጠኝነት የተሞላበት አመራር መስጠት፡

ለ. በኤጀንሲው የሥራ ቦታዎች ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚነደፉ እቅዶችን ፕሮግራሞችን የስርዓተ ፆታ እኩልነትንና ልዩ ትኩረት የሚሹ ሠራተኞችን ያገናዘቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

ሐ ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተነደፉ እቅዶችና ፕሮግራሞች ከዝግጅት ጀምሮ እስከ አፈፃፀም የሚኖራቸው አጠቃላይ ሂደት ግልጽነት /አሳታፊነት/ፍትሐዊነትና ተጠያቂነት የሰፈነባቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፡

መ. የኤች አይቪ/ኤድስ ፈንድ ማቋቋም. በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን መከታተል፤

ሠ. የፈንዱን የወጪና የገቢ ጊዜዉን ጠብቆ ኦዲት መደረጉን ማረጋገጥ፤

ረ. ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ ካለና ከኤድስ ህሙማን ሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ድጋፍና እንክብካቤ በአጠቃላይ ከፀረ ኤች አይቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ጥቆማዎች፣ አቤቱታዎችና ቅሬታዎችን ተቀብሎ ውሳኔ መስጠት፣

6.3 የኤጀንሲው **ዝቅተኛ አመራር** የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ. የኤች አይቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለና የኤድስ ሕሙማን ሠራተኞች በሥራ ቦታዎች ሰብዓዊ መብታቸው የተከበረ መሆኑን ተገቢው ድጋፍና እንክብካቤ መደረጉን ማረጋገጥ፣

ለ ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ ካለና ከኤድስ ህሙማን ሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ድጋፍና እንክብካቤ በአጠቃላይ ከፀረ ኤች አይቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ጥቆማዎች፣ አቤቱታዎችና ቅሬታዎችን ተቀብሎ ውሳኔ እንዲሰጥ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

## 7 የሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

ማንኛውም የኤጀንሲው ሰራተኛ የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

7.2 ለአባላዘር በሽታዎችና ለኤች አይቪ/ኤድስ ከሚያጋልጡ ሁኔታዎች ራሱን በመጠበቅ ለሌሎች መልካም አርአያ መሆን፣

7.3 ኤጀንሲው ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለሚነድፋቸው እቅዶችና ፕሮግራሞች ተግባራዊነት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ፣

7.4 በሥራ ቦታዎች ወሲባዊ ግንኙነት ከመፈፀም መታቀብ፣

7.5 በኤች አይቪ/ኤድስ ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ምክሮችንና ወቅታዊ መረጃዎችን በንቃት የመከታተልና ተግባራዊ ማድረግ፣

7.6 ኤጀንሲው ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚዘረጋቸው አሠራር ላይ በንቃት መሳተፍ፡

7.7 ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ ባለና በኤድስ ህሙማን ሠራተኞች በውሳኔ አሰጣጥ በስራ ግንኙነት፣ በቃላት፣ በድርጊት ወይም በሌሎች ዘዴዎች አድሎና መገለል ከመፈጸም በመቆጠብ ሰብዓዊ መብታቸውን ማክበር፣

7.8 ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚካሄደውን ጥረት ለማሳካት በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሙያ፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣

7.9 ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ይህን ማኑዋል ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን፣

## 8 የኤች አይቪ/ኤድስ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ የሚኖር ሠራተኞች ቫይረሱ በደሙ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሠራተኛ የሚከተሉትን ተግባራትና ኃላፊነቶች የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

8.2 ለአባላዘር ለፀረ፣ ኤች አይቪ ኤድስና ለተጓዳኝ በሽታዎች የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት በአግባቡ በመከታተልና ህመሙን ከሚያባብሱ ደባል ሱሶች በመታቀብ ጤንነቱን የመጠበቅ እና ለኤጀንሲው ተልእኮ የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ ማበርከት፣

8.3 ራሱን ከማግለል ተቆጥቦና ተገቢውን የሥራና የማህበራዊ ግንኙነት ማጎልበት፣

8.4 ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ኤች አይቪን ወደ ሌላ ላለማስተላለፍ ጥንቃቄ በማድረግ ሠራተኞችን መላውን ህብረተሰብ ከወረርሽኝ ስርጭት ለመጠበቅ ያለበት ኃላፊነት በተነሳሽነትና በተቆርቋሪ ስሜት መወጣት፣

8.5 እንደማንኛውም ሠራተኞች አግባብ ያለውን ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ለማክበር የመስራት፣

8.6 በኤች.አይቪ/ኤድስ ዙሪያ ያለውን ተሞክሮ በፍቃደኝነት የግብረ ኃይሉ አባል በመሆን ለሠራተኞች ግንዛቤ በመስጣት አርአያ መሆን፣

## 9 የፀረኤች አይቪ/ኤድስ ግብረ ኃይል መቋቋም፣

በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰየም የፀረ ኤች አይቪ/ኤድስ ግብረ ኃይል በዚህ ማኑዋል ተቋቁሟል፡፡

## 10. የፀረ ኤች አይቪ/ኤድስ ግብረ ኃይል አባላትም አሰያየም ግብረ ኃይሉ፡-

10.1 ሰብሰቢውን ጨምሮ ከየሥራ ሂደቱ በዋና ዳይሬክተር የሚሰየመው አባላት፣

10.2 በዋና ዳይሬክተር የሚመደብ የሥራ ሂደት/ የሥራ ክፍል

10.3 ከዋና መ/ቤት ከሠራተኞች ከሶሻል ኮሚቴ አንድ ተወካይ አባል ይሆናል ፣

10.4 ፍቃደኛ በመሆን ራሱን ያሳወቀ ኤች አይ ቪ ቫይረሱ በደሙ ውስጥ የሚገኝ ከሠራተኛ አንድ አባል፣

## 11. ስለ ግብረ ኃይሉ የሥራ ዘመን

የግብረ ኃይሉ አባላት የሥራ ዘመን 2(ሁለት) ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም አባሉ ለተጨማሪ 2(ሁለት) ዓመት ሊመደብ ይችላል፡፡

## 12. የፀረ ኤች አይቪ/ ኤድስ ግብረ ኃይል ተግባርና ኃላፊነት

የፀረ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ግብረ ኃይል ተጠሪነቱ ለዋና ዳይሬክተር ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

12.1 የብሔራዊ ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠሪያ ፖሊሲ የሥራ ቦታ የኤች አይ ቪ/ኤድስን መከላከልና መቆጣጠሪያ መመሪያ ፣ኤች አይቪ ኤድስን የሚመለከቱ ሌሎች የፌደራል መንግስት ሕጎችና ይህ ማኑዋል በኤጀንሲው ውስጥ እንደ አግባቡ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

12.2 የሥራ መርሃ ግብር እና አመታዊ ረቂቅ ዕቅድ ይዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

12.3 በኤጀንሲው የሥራ ቦታዎች የኤች አይቪ /ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ የሙያ የቴክኒክ የቁሳቁስና የፋይናንስ እገዛ የሚገኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

12.4 የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ያለ እና የኤድስ ህሙማን ድጋፍና የእንክብካቤ አገልግሎት ስለሚያገኙበት ሁኔታ ወይም አገልግሎቱ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ በሚቀርብ ኃሳብ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

12.5 የኤች አይቪ ፈንድ ስለሚዳብርበት ሁኔታ በማጥናት ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት ያደርጋል፡፡

12.6 ግብረ ኃይሉ የሚመራበትን የአሰራር ማኑዋል ሊያዘጋጅ፣ በኤጀንሲው ከፍተኛ አመራር ሲፀድቅም በሥራ ላይ ያውላል፡

12.7 ከኤጀንሲው የበላይ ኃላፊ የሚሰጡትን ሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮች ያከናውናል፡፡

## 13. ስለግብረ ኃይሉ ስብሰባዎችና የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት፣

13.1 የፀረ ኤች አይቪ /ኤድስ ግብረ ኃይል ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፡ሆኖም አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም የኤጀንሲው የፀረ ኤች አይቪ ኤድስ የሚወከል የሥራ ሂደት/ የክፍል በሚያቀርበው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

13.2 ግብረ ኃይሉ በዚህ ማንዋል በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ውሳኔ በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ በጋራ ስምምነት ውሳኔ ያስተላልፋል፣ሆኖም በአባላቱ መካከል የሀሳብ ልዩነት ሲያጋጥም በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፡፡ የተሰጠው ድምፅ እኩል በእኩል ሲሆን በኤች አይ ቪ ግብረ ሃይል ሰብሰቢ እና በሰብሳባው የተደገፈው ሃሳብ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

13.3 ግብረ ሃይሉ የፈንዱን አቅም በማየት በከፍተኛ አመራር በማማከር ድጋፉን መጠን መጨመርም መቀነስም ይችላል፡፡

## 14. የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ዳይሬክተር ተግባር እና ኃላፊነት፣

የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

14.1 ኤችአይቪ/ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር በተለያየ የሥራ ሂደቶች የሚነድፉት ፕሮግራሞችና እቅዶች ያቀናጀል የሚደረጉ ጥረቶችን ያስተባብራል፣

14.2 በኤች አይቪ/ ኤድስ ዙሪያ የሚወጡ ወቅታዊ መረጃዎችን በማሰባሰብ በማደራጀት፣ በማጠናቀርና በማሰራጨት ሠራተኞች እንዲያውቋቸው ያደርጋል፡፡

14.3 ኤችአይቪ/ ኤድስ በኤጀንሲው እያደረሰ ያለውን ተጽእኖ እያጠና ተገቢው እርምጃ እንዲወስድ ለግብረ ኃይሉ ሃሳብ ያቀርባል፣

14.4 በኤች አይቪ/ኤድስ ዙሪያሥልጠና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እያቀናጀ ተግባራዊ ያደርጋል፣ኤች አይቪ/ኤድስን በተመለከተ የሚሰጡ ትምህርትና ሥልጠናዎች በተለይ ለበሽታ ተጋላጭ የሆኑትን ሴት ሠራተኞችና የአካል ጉዳተኞች ያገናዘበ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

14.5 ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለሚወጡ እቅዶች ማስፈፀሚያ የሚውል የሀብት ምንጭ የሚገኝበትን መንገድ ያፈላልጋል፡፡

14.6 ኤች አይቪ/ኤድስን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን ህጎችና መመሪያዎችንየኤጀንሲው ሠራተኞችእንዲያውቋቸው ያደርጋል፡ መተግበራቸውንም ይከታተላል፣ይገመግማል፤

14.7 በኤች አይቪ/ኤድስ ዙሪያ ከሚሠሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከሌሎች አካላት ጋር በአጋርነት ይሠራል፡፡በሪጅን ና በቅ/ጽ/ቤት የተቋቋሙት የኤች አይ ቪ ኤድስ ግብረ ሀይል ይከታተላል፣ ያስተባብራል. ይገመግማል ፣የሥልጠና ሥርዓቶችን እያቀናጀ ተግባራዊ ያደርጋል፣ኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ በደማቸው የሚገኝ ሠራተኞች ሚስጥራቸውን በመጠበቅ ክትትል ያደርጋል፣

14.8 ኤች አይቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጡ ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን አፈፃፀምን በተመለከተ የክትትልና የግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፡፡

14.9 ድጋፍ ስለሚያስፈልጋቸው የኤድስ ህሙማን እያጠና ከግብረ ኃይሉ ጋር ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

14.10 ኤች አይቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለ የኤጀንሲው ሰራተኞች ገንዘብ ነክ ከሆኑ ድጋፎች ውጪ የድጋፍ አገልግሎት ሲጠይቁ ሚስጥሩ በስራ ሂደቱ/ ክፍል ብቻ ተይዞ በተለያዩ የሥራ ቦታ ላይ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

14.11 ከኤች አይቪ/ኤድስ ግብረ ሀይል ጋር ተቀናጅቶ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮችንም ያከናውናል፡፡

14.12 የግብረ ኃይሉ ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 15. የኦዲት ዳይሬክቶሬት ተግባርና ኃላፊነት

የኦዲት ዳሬክቶሬቱ ተጠሪነቱ ለኤጀንሲው ለከፍተኛ አመራር ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነት ይኖሩታል፡

15.1. የፀረ ኤች አይ ቪ ግብረ ኃይሉን የሥራ አፈፃፀም በየ3 ወሩ ይገመግማል የአሠራር ግድፈቶች ሲኖሩ የመፍትሄ እና የአሠራር ማሻሻያ /ማስተካከያ/ ሃሳቦችን ያቀርባል፣

15.2. የፈንዱን የገቢ እና የወጪ ሒሳቦችን ይመረምራል፤

15.3. በየ6 ወሩ ስለ ፈንዱ የፋይናንስ እና ሥራ አፈፃፀም እንቅስቃሴ ለከፍተኛ አመራር ሪፖርት ያቀርባል፣

15.4. ለግብረ ኃይሉ ጠቃሚ የሆኑ የሂሳብ እና የንብረት አያያዝ ስልቶችን ይቀይሳል፡፡

## 16. የሠራተኞች መብት

16.1 የኤች አይቪ/ኤድስ የተወከለው ስራ ሂደት/ክፍል እና ግብረ ሀይል በሚነድፏቸው እቅዶችና ፕሮግራሞች በሚሰጧቸው አገልግሎቶች እኩል ተሳታፊ መሆን፡፡

16.2 ከኤች አይ ቪ/ኤድስ የተወከለው ስራ ሂደት/ክፍል እና ግብረ ኃይሉ በሚዘጋጇቸው የምክክር ስብሰባዎች ስልጠናዎችና ፕሮግራሞች ላይ የመካፈል፤

16.3 የኤች አይቪ/ኤድስ የተወከለው ስራ ሂደት/ክፍል እና የግብረ ኃይሉን አጠቃላይ አሰራር ወይም የኤች አይ ቪ/ኤድስ ፈንድ አጠቃቀም ግልፅ እንዲሆንላቸው የመጠየቅ ማብራሪያ የማግኘትና የማወቅ፣

16.4 የኤችአይቪ/ኤድስ የተወከለው ስራ ሂደት/ክፍል እና ግብረ ኃይሉ አጠቃላይ አሠራር ወይም የኤች አይቪ ኤድስ ፈንድ አጠቃቀም ግልጽ እንዲሆንላቸው የመጠየቅ ማብራሪያ የማግኘትና የማወቅ

16.5 በጾታ፣ በአካልጉዳት በኢኮኖሚ ወይም በማህበራዊ ችግሮች ምክንያት ከኤች አይቪ/ኤድስ ተገላጭነት ጋር በተያያዘ የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥመው ይህንኑ በማስረዳት ልዩ ድጋፍ የመጠየቅ፣

16.6 ኤች አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ በተወከለው ስራ ሂደት/ክፍል እና በግብረ ኃይሉ ይዞታ ስር የሚገኙ መረጃዎችን ለአጠቃቀም አመቺ በሆነ መንገድ የማግኘት፣

16.7 የተወከለው ስራ ሂደት/ክፍል እና በግብረ ሀይሉ አሠራርና በፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴ የአፈፃፀም ሂደት ቅር ሲሰኝ አቤቱታ የማቅረብና የመደመጥ፣

16.8ማንኛውም ሠራተኛ በሙሉ ነፃ ፈቃደኝነት የኤች አይ ቪ/ኤድስ ምርመራ እንዲያደርግ ይበረታታል ሆኖም የምርመራው ውጤት ይፋ እንዲያደርግ አለመገደድ፣

16.9 የኤች አይ ቪ የምርመራ ውጤትና መረጃዎች ጥብቅ ሚስጥር ሆነው ይያዛሉ፤ይፋ ሊደረጉ የሚችሉት ተመርምሮ ውጤቱን ባቀረበው ሠራተኛ ነጻ ፍቃድና የጽሁፍ ስምምነት ብቻ ይሆናል፡፡

16.10 የኤች አይ ቪ በደም ውስጥ ቢኖርም በትምህርትና ሥልጠና፣ በደረጃ እድገት፣ በድልድል፣ በምደባ ጊዜ እድሉ ሳይደረግበት ተሳታፊ እና ተጠቃሚ መሆን፣

## 17 ስለዝውውር

17.1የኤድስ ሕመምተኞች የሆኑ ማናቸውም የኤጀንሲው ሠራተኞች የተመደቡበትን የሥራ መደብ ተግባርና ኃላፊነት በሚገባ ለመፈፀም የመሥራት አቅማቸው ሲደክም የያዙት ደመወዝ ሳይቀነስባቸው በራሳቸው ስምምነት አቅማቸው ወደ ሚፈቅደው የስራ መደብ ተዛውረው እንዲሰሩ የሚቻለውን ጥረት ሊያረግ ይችላል፡፡

17.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) በተጠቀሰው ምክንያት ሆነ አግባብነት ባላቸው የፌደራል መንግስት ሠራተኞች ሕጎች መሠረት ዝውውር ሲፈጸም ኤች አይቪ በደማቸው ውስጥ ያለ ሠራተኞችን ለተጓዳኝ በሽታዎች በሚያጋልጡ የሥራ ቦታዎች ላይ አዛወሮ ማሰራት የተከለከለ ነው፡፡ ለዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም ሲባል የሚዛወሩበት የስራ ቦታ ለተጓዳኝ በሽታዎች የማያጋልጥ መሆኑ ከዝውውሩ በፊት መረጋገጥ አለበት፡፡

## 18 ስለ ሥራ ዋስትና

18.1 . ሠራተኞቹ በህግ አግባብነት ካልሆነ በቀር ኤች አይቪ በደማቸው ውስጥ በመኖሩ ወይም የኤድስ ህመምተኛ በመሆናቸው ምክንያት የስራ ውል አያቋርጥም የሚያገኟቸውም ጥቅማ ጥቅሞቹ አይቀሩባቸውም፡፡

18.2 በሠራተኛ ቅነሳ ወቅት በህግ አግባብ ካልሆነ በቀር ሠራተኞች ኤች አይ ቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ በመኖሩ ወይም የኤድስ ሕመምተኛ በመሆናቸው ምክንያት ከስራ አይቀንሱም፤

# ክፍል ሦስት

## ስለ ፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ፈንድ መቋቋም ድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ

## 19 ስለ ፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ፈንድ መቋቋም

የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የፀረ ኤች አይቪ ፈንድ በዚህ ማኑዋል ተሻሽሎ ተቋቁመዋል፡፡

## 20. ስለ ፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ፈንድ ምንጮች

የፀረ ኤች አይ ቪ ፈንድ የገቢ ምንጭ ከሠራተኛው ከሚሰበሰበው መዋጮ እና ከሌሎች ከተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች ከሚገኝ ገንዘብ ይሆናል፡፡

## 21.ፈንድን ስለማስተዳደር

የፀረ ኤች አይ ቪ ፈንድ የሚያስተዳድረው የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት እና በዚህ ማኑዋል የተቋቋመው ግብረ ኃይል ነው፡፡

## 22. ስለ ፈንድ አጠቃቀም

22.1 የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ፈንድ ስራ ላይ የሚውለው በዚህ ማኑዋል ለተጠቀሱት ድጋፎች ብቻ ይሆናል፡፡

22.2 የፈንዱ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በግብረ ሀይሉ ሰብሳቢ፣ በከፍተኛ አመራር የሚሰየም ከግብረ ሀይሉ ሁለት አባል፣

22.3 ከፈንዱ የባንክ ሂሳብ የሚወጣው በተራ ቁጥር 22.2 በተጠቀሱት የጣምራ ፊርማ ሆኖ ከሦስቱ በሁለቱ ብቻ ገንዘብ ማውጣት ይችላል፡፡

## 23. ስለድጋፍና እንክብካቤ

ኤጀንሲው እንደሁኔታው ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱን ወይም ከአንድ በላይ ድጋፍና እንክብካቤ በነጠላ ወይም በጣምራ ሊሰጥ ይችላል

ሀ. ወርሃዊ የገንዘብ ድጎማ፣

ለ. ለአንድ ጊዜ ወይም በተከታታይ ወይም እንደ አመቺነቱ በየወቅቱ የሚደረግ የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ፣

ሐ. ዘላቂነት ያለው የአንድ ጊዜ ማቋቋሚያ፣ በአይነት ወይም በገንዘብ ድጋፍ፣

መ. የምግብ፣ የአልባሳት፣ የህክምናድጋፍ፣

ሠ. የቤት ለቤት እንክብካቤና የምክር አገልግሎት ድጋፍ፣የፀረ ኤች አይ ቪ/ኤድስ የተወከለው ስራ ሂደት/ክፍል እና ግብረ ሀይል እንደነገሩ አግባብነት በየጊዜው እያጠኑ የሚወስኑት ሌሎች የድጋፍና እንክብካቤ አይነቶች፣

## 24. ድጋፍና እንክብካቤ የማድረግ ኃላፊነት

ኤጀንሲው አቅም በፈቀደ መጠን በዚህ ክፍል ውስጥ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ድጋፍና እንክብካቤ ያደርጋል፡፡

## 25 ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላቸው ሠራተኞች

በኤጀንሲው ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረግላቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

25.1 ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ ያለና የኤድስ ህሙማን ሠራተኞች፣

25.2 ድጋፍ ሲደረግላቸው የነበሩና በህመሙ ምክንያት በጣም ታመው የስራ ውላቸው የተቋረጠባቸው

## 26. ድጋፍና እንክብካቤ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ሁኔታዎች፤

26.1 በዚህ ማኑዋል አንቀጽ 2(2) በተገለፀው መሠረት ኤች አይ ቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለ ወይም የኤድስ ህመምተኛ ለሆኑ የአጀንሲው ሠራተኞች ድጋፍና እንክብካቤ የሚደረገው፡-

ሀ. ድጋፍና እንክብካቤ እንዲደረግለት ለፀረ ኤች አይ ቪ/ ኤድስ ለተወከለው የሥራ ሂደት/የሥራ ክፍል ጥያቄ ሲያቀርብና መረጃው ተቀባይነት ሲያገኝ፣

ለ. ሠራተኛው ኤች አይቪ/ ኤድስ በደሙ ውስጥ ለመኖሩ ወይም የኤድስ ህመምተኛ ለመሆኑ ሕጋዊ እውቅና ካለው የህክምና ተቋም የህክምና ማስረጃ ሲያቀርብ፣

ሐ. የቅርብ አለቃው መረጃውን ከዋናው ጋር አያይዞ በደብዳቤ ሲልክ

መ. ድጋፍና እንክብካቤ ማግኘት የሚገባው ወይም የሚያስፈልገው መሆኑ በግብረ ኃይሉ ሲታመንበት፣

## 27. የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ፡-

በዚህ ማኑዋል መሠረት የኤችአይቪ/ኤድስ ታማሚ በመሆኑ ምክንያት ለሠራተኛው የሚደረግ የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥ በሚከተለው ሥርዓት መሠረት ይፈፀማል፤

ሀ. ሠራተኛ የኤችአይቪ ኤድስ ታማሚ/ በሽተኛ መሆኑን

ለ. ከኤችአይቪ ፈንድ የገንዘብ ድጋፍ የሚያስፈልገው መሆኑን በጽሁፍ በመግለጽ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 26(1) (ለ) ላይ በተደነገገው መሠረት የቫይረሱ ታማሚ መሆኑን ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ ህጋዊ ማስረጃ ሲያቀርብ፣

ሐ. ድጋፍ እየተደረገለት የነበረ ሠራተኛ በሞት ሲለይ ለቤተሰቦቹ የ3 ወር ድጋፍ አንድ ጊዜ ከተደረገ በኃላ ድጋፉ ይቋረጣል፡፡

## 28. የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥን ስለማሳወቅ

የድጋፍና እንክብካቤ አሰጣጥን በሚከተለው አኳኋን ይፋ ያደርጋል፡፡

28.1 ማኑዋልን ለሠራተኞች በማሳወቅ፣

28.2 በመሥሪያ ቤቱ ሰሌዳዎች ማስታወቂያ በመለጠፍ፣

28.3 በስራ ሂደት ባለቤቶች በኩል ለሠራተኞች በማሳወቅ፣

## 29. ድጋፍና እንክብካቤ ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

ድጋፍና እንክብካቤ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ውስጥ ቢያንስ በአንዱ ምክንያት ሊቋረጥ ይችላል፣

29.1 ድጋፍና እንክብካቤ እንዲቋረጥ ሠራተኛው በጽሁፍ ሲጠይቅ

29.2 ድጋፍና እንክብካቤውን ለመጀመር ምክንያት የነበረው የኢኮኖሚ ወይም ከኤችአይቪ/ ኤድስ ጋር የተያያዘ የጤና ወይም ሌላ ችግር የተወገደ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

29.3 ድጋፍና እንክብካቤ ሲደረግ የቆየው በሐሰት ማስረጃ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

29.4 ድጋፍ እና እንክብካቤ የሚደረግለት ሠራተኛ በሞት ሲለይ፣

29.5 የኤጀንሲው ኤችአይቪ /ኤድስ ፈንድ አቅም ድጋፍና እንክብካቤውን ለማስቀጠል የማያስችል ሲሆን፣

29.6 የእርዳታው ተጠቃሚ የሕክምና ትዕዛዝ የማይቀበል ሲሆን፣

## 30. ከኤች አይቪ /ኤድስ ጋር የተያያዙ የዲሲፒሊን ጥፋቶች

በሥራ ቦታዎች ኤች አይቪ /ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲቻል የመንግስት ሠራተኞች መህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ሥነ-ምግባር መመሪ አንቀጽ 28 ንዑስ (1) እና (2) ሥር የተዘረዘሩትን ድርጊቶች መፈፀም ከቀላል እስከ ከባድ የዲሲፒሊን ጥፋቶች ይሆናሉ፡፡

30.1 ኤጀንሲው ኤች አይቪ /ኤድስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ሆን ብሎ ማወክ፣

30.2 በስራ ቦታዎች ወሲባዊ ጥቃቶች መፈፀም ወይም ለመፈፀም መሞከር

30.3 ሠራተኞች ወይም ሥራ ፈላጊ አመልካቾች የኤች አይቪ /ኤድስ ምርመራ እንዲያደርጉ ወይም በነፃ ፍቃዳቸው ያደረጉትን የኤችአይቪ /ኤድስ የምርመራ ውጤት ይፋ እንዲያደርጉ ማስገደድ፣

30.4 በሥራ ምክንያት ያወቀውን የሠራተኞችንና የሥራ ፈላጊ አመልካቾችን ኤች አይ ቪ ምርመራ ውጤት ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ የህክምና መረጃ በሥራው አስገዳጅነት ምክንያት መግለጽ ከሚገባው ውጭ ያለግለሰቡ የጽሑፍ ስምምነት ለሌላ ሰው ይፋ ማድረግ፣

30.5 ኤች አይ ቪ /ኤድስ በደሙ ውስጥ በመኖሩ ወይም የኤድስ ህመምተኛ በመሆኑ ምክንያት በትምህርትና ሥልጠና፣ በደረጃ እድገት በዝውውር በድልድልና በስራ ዋስትና ወይም በሌላ ሥራ ሁኔታ ረገድ በማንኛውም ሠራተኛ አድሎና ልዩነት መፈጸም፣

30.6 ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በሥራ ቦታዎች ኤችአይቪ /ኤድስን ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍ የሚያስችል ድርጊቶች መፈጸም፣

30.7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (6) ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ የሆነ አድሎአዊ አሰራር ወይም ሕገ ወጥ ድርጊት መፈፀም፣

## 31. ስለዲሲፒሊን ክስ አቀራረብና ስለውሳኔ አሰጣጥ

31.1 በዚህ ማኑዋል አንቀጽ 30 የተመለከቱት ድርጊቶች የተፈፀመበት ማንኛውም ሠራተኛ ለኤጀንሲው ለከፍተኛ አመራሩ በጽሁፍ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፥

31.2 የኤጀንሲው ከፍተኛ አመራር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የቀረበለት ጉዳይ ሊጣራ የሚገባ መሆኑን ሲያምንበት አቤቱታ በቀረበበት ሠራተኛ ስለፈፀሙ ተጣርቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ በኤጀንሲው ለተቋቋመው የዲስፒሊን ኮሚቴ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 32. ስለ ዲፒሲሊን ቅጣት

በዚህ ማኑዋል አንቀጽ 30 (1) ከተመለከቱት ጥፋቶች ቢያንስ አንዱን ፈጽሟል ተብሎ ክስ የቀረበበት ሠራተኛ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ 1064/2010 አንቀፅ 69(1) ሥር ከተመለከቱት የዲሲፒሊን ቅጣቶች መካከል አንዱን ይቀጣል፡፡

## 33. ከማኑዋሉ ጋር የሚቃረኑ ሕጎችና አሠራሮች

32.1 ይህ ማኑዋል የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው የፌደራል መንግስት ሠራተኞች የሥራ ቦታዎች የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠር ማኑዋል ጋር የሚቃረን ወይም ክፍተት ያለው ሆኖ ሲገኝ የፌደራል መንግስት ሠራተኞች የሥራ ቦታዎች የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ማኑዋል ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

32.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህን ማኑዋል የሚቃረን ማኑዋል አሠራረርና ልምድ በዚህ ማኑዋል ውስጥ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 34. ማኑዋልን ስለማሻሻል

ይህ ማኑዋል እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ ስሰያፈልግ በህጻናትና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት እና የፀረ ኤች አይቪ ግብረ ኃይል ለኤጀንሲው ከፍተኛ አማራር ኃሳብ በማቅረብ ማኑዋልው በሙሉ ወይም በከፊል እንዲሻሻል ማድረግ ይቻላል፡፡

**35. ማኑዋሉ የሚጸናትበት ጊዜ** *ከኅዳር1/ 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል*

***አቶ ዳባ ኦሪያ***

***ፊርማ***

***የመንግስት ሠራተኞች ማህባራዊ ዋስትና ኤጀንስ ዋና ዳይሬክተር***

***አዲስ አበባ***

*ኅዳር 2013 ዓ.ም*